# <u>አለን ባመፅ</u> (ቁጥር ስድስት) (ከአጅሬው ዝብርቅርቅ ማህደር)

**ካለፈው የቀጠለ**

## <u>ክብረት ሞላ</u>

ስለክብረት መናገር ስጀምር ልክ ስለፀሐይ ንጉሴ መናገር እንደጀመርኩት አድርጌ ቅደም ተከትል እንዳላወጣሁለት በአእምሮየ የመጣውንና የማስታዉሰውን ብቻ እንደማወራው በተቻለ መጠን የገዳይ የአጋዳይ ስሞቹን ሳልጠቅስ የራሴንም ስሜት ለራሴ አስቀርቼ እንደምተርክለት ነግሬው ግን ታሪኩ ጠንከር ያለ ሂደት እንደነበረው አስረድቸው ነበር ታሪኩን የተረኩለት።

የክብረት አገዳደል ፍጥነት የሞላው ነበር። ታውቅ አታውቅ እንደሆን አላውቅም እንጂ ክብረት የወታደር ልጅ ነው (ነበር አልልም አሁንም ህያው ነውና)። አባቱ ኮርያ ይሁን ኮንጎ ወይም ሁለቱም ቦታ የዘመቱ አምሳ አለቃ ናቸው። ልጃቸው እንደጠፋ ያወቁት በተያዘ ማግስት ነበር። ከሰፈር ባልንጀሮቻቸውና ቤተዘመዶቻቸው ጋር በመሆን ወደሶስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ቢሄዱ የለም ተባሉ። አብረዋቸው ለሄዱት ሰፈረተኞች አንዱ በሰፋራቸው ኖሪ የሆነ ፓሊስ ማታ ጣቢያ አምጥተውት ሌሊቱን እንደወሰዱት በመጠቆሙ ከጊዜው ጋር በተያያዘ የሰፈር ሰዎች ተሽቀዳድመው ወደምኒሊክ ሆስፒታል የሬሳ ቤት ሄዱ። ሬሳ ቤት የሚገባ ደፋር ቶሎ የክብረት ወላጆችና ቤተዘመዶች ሳይመጡ ተባለና አንዱን ወጣት አንተ ግባ አንተ ግባ ተብሎ ከሬሳወች መካከል አንገቱን አርደውት ሬሳውን አይቶ እየተንቀጠቀጠ ወጥቶ ለሰፈረተኞቹ ነገረ (ይህ ወጣት ከተገደሉ ወጣቶች መካከል የክብረትን መኖርና አለመኖር ለመለየት ሲሞክር በተመለከተው የተነሳ ለብዙ ጊዜ የአእምሮ ታማሚ ሆኖ ነበር በኋላም ራሱን አንቆ ገደለ)። ቤተሰቦቹን የለም ብሎ ወደቤታቸው የሚመልስ መላና መልዕክተኛ አዘጋጅተው ወደሰፋራቸው ተመልሰው ድንኳን በፍጥነት አስጣሉ። ድንኳኑ በለቀስተኛው ሞልቶ ዋይ ዋይታው ቀጥሎ ሬሳውን ከዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል እንዲያመጡ ስራ የተሰጣቸው ሰዎች በወቅቱ ለተገደል “አናርኪስት” የሚከፈለውን ገንዘብ (ለጥይት መሆኑ ነው፤ ነገር ግን ክብረት የተገደለው በጥይት ሳይሆን አንገቱን ቆርጠውት ነው) ከፍለው ሬሳውን አምጥተው ከቤት አረፈ። አመሻሽ ላይ ከመኝታ ቤታቸው ሳይወጡ የቀሩት አባቱ አምሳ አለቃ ሞላ ይሁኔ ወደ ድንኳኑ መጥተው መንቆራጠጥ ጀመሩ።

“ፈሪ!” “ፈሪ ሁላ!” “ምድረ ፈሪ!” የአገር ፈሪ ብቻ ፊት ለፊት አይገጥሙም። “የፈሪ ልጅ ሁላ ተሹም ተሹሞ። ፊት ለፊት አይገጥሙም”። “ትልቅ ሰው ለትልቅ ሰው አይገጥሙም”። “ጨቅላ እየፈለጉ መግደል. . . ”። ልጄ የሕዝብ ልጅ ነው! ልጄ ጀግና ነው ልጄ ለአገሩ ነው የሞተው . . . ልጄ! ልጄ! ልጄ! ልጄ! ልጄ! እያሉ ለቅሶም ንግግርም እየቀላቀሉ በኮራሁበት አገር፣ በተዋጋሁለት አገር፣ በምወደው አገር፣ በተከበርኩበት ሰፈር፣ በተደሰትኩበት መንደር፣ የጄን ሬሳ ታቀፍኩበት፣ የልጄን ሞት አየሁበት፣ ለልጄ ሞት አለቀስኩበት። ብለው ከጨኸታቸው በረድ ብለው ከተደረደሩት ወንበሮች አንዱን ደገፍ ብለው አጎንብሰው ትንሽ ዝም አሉና በተሰበረ የትልቅ ሰው ድምፅ አይናቸውን ጨፍነው ልጄ! ልጄ! ልጄ! እንቀያየር እኔን ይግደሉኝ አንተ ገና ነህ። እባክህን ሞት ተለመነኝ ልጄን መልስና እኔን ውሰደኝ ይሉና ስቅስቅ ብለው አልቀሰው የተደገፉት ወንበር ላይ ውዝፍ አሉ። የሳቸውን የአዛውን ድምፅ የሰማ ለቀስተኛ ድንኳኑን በእየየ አደባለቀው። ዝምታቸው ሲበቃቸው እንደገና ተነስተው መንቆራጣጠቸውን ቀጠሉ። ማን ነው ልጄን ያስገደለው? ማን ነው ልጄን የጠቆመው? ማን ነው ባንዳው? ማን ነው ጣሊያን ትቶት የሄደው አይጥ? . . . እያሉ ወጣቶች ጠርቀም ብለው ወደተቀመጡበት ከባቢ በመምጣት ድንኳኑ ውስጥ የተሰበሰቡትን ወጣቶች ላይ ተራ በተራ አፈጠጡ። ሁላችሁንም አውቃችኋለሁ። ሁላችሁም ልጆቻችን ናችሁ። ሁላችሁም ከልጄ ክብረት ጋር አብሮ አደጎች ናችሁ። ሁላችሁም የአንድ ቀየ ልጆች ናችሁ።

ከግማሾቻችሁ ወላጆች ጋር ለአገራችን አብረን ዘምተን ተዋግተናል። ከከፊሎቻችሁ ወላጆች ጋር በሃዘንም በደስታም አብረን ለአመታት ኖረናል። የእኛም ወላጆች አብረው ከጣሊያን ተዋግተዋል። እንዴት እንዴት ምን ሲደረግ ወንድማችሁን አብሮ አደጋችሁን ታሳርዳላችሁ አሉና ወየው ኢትዮጵያ ወየው አንቺ አገር ወየው ወየው። ልጅ ቢያጠፋ ይቀጣል እንጂ ይታረዳል ብለው ድንገት መሬት ላይ ሽርተት ብለው በመውደቅ ለመግለፅ በሚቸግር አይነት ድምፅ በልባቸው ተደፍተው ስቅስቅ ብለው አለቀሱ። ቤተዘመድና ጎረቤት ትላልቅ ሰዎች በግድ ተቆጥተው ጐተተው ወደ ቤት አስገቧቸው።

የክብረት እናት ወይዘሮ እቴነሽ ባልቻ ከድንኳኑ መካከል ለቤተዘመድ ከተነጠፈው ፍራሽ ላይ ተቀምጠው ይወዘወዛሉ። ጠይምነታቸው ላይ ሃዘን ሳይሆን በህይወት ሳይኖሩ መተንፈስ ይታይባቸዋል። አያለቅሱም፣ አይጮኹም፣ አይናቸው አይርገበገብም፣ የሰውነት ንቅናቄ የላቸውም። የተቀመጠ በድን ሰው መስለዋል። ወዳጅ ዘመድና መንደረተኛው መክሮ በቶሎ ክብረትን መቀበር እንደሚገባ በወሰኑት መሰረት በማገስቱ ንጋት የከባቢው እድር ጡሩንባ ነፊ ሰፈሩን እየዞረ "በእንትን አካባቢ የምትገኙ የእንትን ነዋሪዎችና እድርተኞች የአምሳ አለቃ ሞላ ይሁኔ ልጅ ክብረት ሞላ ስላረፈ አቃብሩኝ ብለዋችኋል መቃብሩም እንትን ቤተክርስቲያን ነው" ብሎ ለፈፈ። ለቀብሩ የወጡት ወጣቶች፣ አዛውንቶች፣ አሮጊቶች ብዛት እጅግ ብዙ ነበር። ሬሳው ወደ ቤተ ክርስቲያኑ እየቀረበ ሲመጣ ወጣቶች በካባቢው የተገደሉትን ወንድሞቻቸውን ስም እየጠሩ የተቃውሞ መዝሙር መዘመር ጀመሩ።

ክብረት ለምን ለምን ሞተ
ጌታቸው ለምን ለምን ሞተ
በሃይል በትግል ነው ነፃነት የሚገኘው
ሲሳይ ለምን ለምን ሞተ
ትርሲት ለምን ለምን ሞተች
በሃይል በትግል ነው ነፃነት የሚገኘው . . .

ወላጆች በሁኔታው ድንጋጤ ተሰምቶቸው ሊፈጠር የሚችለውን ቢያውቁትም ልጆቻቸውን አትዘምሩ ብለው ለማከላከልም አልሞከሩም እንዲያውም ወጣቶቹን ማካበብ ጀመሩ። የክብረት እናት ወይዘሮ እቴነሽ ባልቻ ሌሊቱን ፀጉራቸውን ተላጭተው በጠይምነታቸው ላይ ጥቁር ልብሰ ተከድነው በተከሻቸው ላይ የኢትዮጵያን ባንዲራ ጣል አርገው ባለቤታቸው አምሳ አለቃ ሞላ ይሁኔ ኮርያ ኮንጎ ዘምተው የተሸለሙትን ሜዳልያ ከሙሉ የጦር ሰራዊት ልብሳቸው ጋር ለብሰው ነበር ለቀብር የወጡት። ሬሳው በተክርስቲያኑ ደርሶ ፍታት ካለቀ በኋላ ለቀስተኛው ወደተቆፈረው ጉድጓድ ሲሄድ የተሰበሰው ለቀስተኛ በጩኸት ከባቢውን ሞላው።

ወይ አትልም ወይ ዋይ አትይም ወይ (አለች አልቃሾ በዜማ)
ዋይ ዋይ ዋየ ምነው (ለቀስተኛ ተቀበላት)
ክብረቱ ልጅሽ ሞቷ የለም ወይ
ዋይ ዋይ ዋየ ምነው

አፈር አፈር አፈር
አሁን ለነማን ትቀር . . . ይሆን (አለች አልቃሾ በዜማ)
አረ ጀግናው ሄደ
አረ ጀግናው ሄደ (ህዝብ ተቀበላት)
የጭቁን ነፃነት

አረ ጀግናው ሄደ (ህዝብ ተቀበላት)
ለማየት ወደደ
አረ ጀግናው ሄደ (ህዝብ ተቀበላት

እናቶች ደረት እየደቁ ወደ ላይ ብድግ ብድግ አሉ። መሬቱን በእግራቸው እየደበደቡ ዘለሉ

አልቅሽ ኢትዮጵያ
አረ ጀግናው ሄደ (ህዝብ ተቀበላት)
እናት አገር ለምለም
አረ ጀግናው ሄደ (ህዝብ ተቀበላት)
ልጅሽ ተቀጠፈ
አረ ጀግናው ሄደ (ህዝብ ተቀበላት)
የሚናገር የለም

ለቀስተኞች የቀብሩን ስነ ስርአት በሙሉ ሃዘን በማክያካሄድ ላይ እያሉ መትረየስ የጠመዱ አራት ግልጥ መኪናወች (በወቅቱ ጂፐ ተብለው የሚጠሩት) ደምፃቸውን አጥፍተው መጥተው አፈሙዛቸውን ወደ ለቀስተኞች ደግነው ራቅ ራቅ ብለው ቆሙ። ሙሾ አውራጇ ሙሾዋን ማውረዱን አከረረችው ለቀስተኞቹ ያፈጠጡባቸውን አፈሙዞች በጐሪጥ አይተው ከቁብ ሳይቆጥሩ ሃዘናቸውን ቀጠሉ። እንዴውም የለቅሶው ሃይል ከረረ።

የእንትናየስ እናት
አረ ጀግናው ሄደ (ህዝብ ተቀበላት)
ጆሮሽ ይሰማል ወይ
አረ ጀግናው ሄደ (ህዝብ ተቀበላት)
ልጅሽ አፈር ሆኖ
አረ ጀግናው ሄደ (ህዝብ ተቀበላት)
ይጣራ የለም ወይ
አረ ጀግናው ሄደ (ህዝብ ተቀበላት)
የእንትናየስ እናት
አረ ጀግናው ሄደ (ህዝብ ተቀበላት)
ልጅሽ ለደሃ ሲል
አረ ጀግናው ሄደ (ህዝብ ተቀበላት)
ተሰዋ አደለም ወይ
አፈር አፈር አፈር
አሁን ለነማን ትቀር . . . ይሆን
እግዚኦ ኡ ኡ በሉ
ላይቀር መንከባለል ካፈር እየራቁ
ጐብዞቹን ፈጁ አገሩን ሊያደርቁ . . . .

እናቶች ደረት እየደቁ ወደ ላይ ብድግ ብድግ አሉ። መሬቱን በእግራቸው እየደበደቡ ዘለሉ . . .

የቀብሩ ስነስርአት ተጠናቀ ለቀስተኞች ወደልቅሶው ቤት ሲመለሱ የወጣቶቹ መዝሙር እንደገና ደመቀ።

አትነሳም ወይ አትነሳም ወይ
የግፍ አገዛዝ አይበቃህም ወይ
ተነስ ተነሽ
እሺ እነሳለሁ እሺ እነሳለሁ . . .

መትረየስ የጠመዱት መኪናወች ቁጥራቸው ከአራት ወደ ስምንት ጨምሮ ከሆላና ከፊት አጅበው ማስፈራራት ቀጠሉ። አዛውንቶችና አሮጊቶች ወላጆች ወጣቶቹን ከልጆቻችን ፊት እኛን ብለው ወደመሃል አካበው አስገቧቸው። ለቅሶው ቤት ሲደረስ ድንኳኑን አስፈርሰው ለቀስተኛውን እርምጃ እንደሚወስዱ አስፈራርተው አምሳ አለቃ ሞላ ይሁኔን እያዳፉ ኮርያ ኮንጎ የዘመቱበትን ኤም ዋን የተሰኘ ጠመንጃ አስገደደው ሲወስዱ። የከተማ እናት ወይዘሮ እቴነሽ ባልቻ ከሰፈረባቸው ድንጋጤ ነቃ አሉና እንቱፍ እንቱፍ ቅ_ናም ሁላ ቅ_ናም ልጄ አልሞተም . . . የውሻ ሞት አልሞተም ልጄ የሕዝብ ልጅ ነው ህዝብ ይፋረዳችኋል . . . የልጄን ሰርግ አላያችሁም እርሙን የበላሁ መሰላቸሁ ህዝብ ሰርጉን ነው የሰረገለት . . . አላያችሁም የሚዜወቹን ብዛት አላያችሁም . . . ልጄን የገደላችሁ መሰላቸሁ እያሉ ሲጮሁ የጠመንጃ ተሸካሚዎቹ አዛዥ ዝም አስኙ ብሎ ወታደሮቹ ላይ ሲጮህ ከልቅሶ የተመለሰው ህዝብ ጋር ከተፋጠጡት ወታደሮች አንዱ የክብረት እናት ወይዘሮ እቴነሽ ከትከሻቸው ላይ ጣል ያረጉትን ባንዲራ ገፎ ባማጅራታቸው ጀብጠ መሬት ላይ ሲደፋቸው ቅ_ናም ሁላ ቅ_ናም ብቻ ልጄ አልሞተም እያሉ ጩኸታቸውን ሲያቀልጡት ከለቅሶ ተመልሶ አሰፍስፎ የቆመ ህዝብ ወደ እነ ክብረት ቤት መታጠፊያ ያለች ቀጭን መንገድ ላይ በመትረየስ ዘግተው አሰገድደው በታተኖቸው፣ ለቀስተኞች ከንፈራቸውን እየነከሱ ተበተኑ . .

እንባየ ተትረከረከ ከፊቴ የተቀመጠው ሰው ጠረንጴዛው ላይ ተደፍቶ ተንሰቅስቆ አለቀሰ። የትግል መሪየ ከሃያ ዘጠኝ አመታት በኋላ መሃል መርካቶ በአጋጣሚ ከፈረንጅ አገር መጥቶ አግኝቸው ልቅሶ ደረሰኝ። የትግል መሪየን ከሃያ አመታት በኋላ መርካቶ በአጋጣሚ አግኝቸው የመራንን ያታገለንን ታጋዮች የመስዋዕትነት ታሪክ ነግሬ አስለቀስኩት። ከብዙ ዝምታ በኋላ ከተደፋበት ቀና ብሎ አተኩሮ እያየኝ "ይቅርታ ተዝረከረኩ" አለና የኔን እንባም መፍሰሱን ሲያይ የተቸገረ ፈገግታ ፈገግ እንደ ማለት ብሎ "ከውስጤ የነበረ የኖረ ቁስል ነው"። "ሃኪም ያማያሽረው፣ ህክምና የሌለው፣ ልቅሶም ደስታም የማያዋጣው ከሰው ልጅ ጭካኔ ውስጥ የፈለቀ የኢትዮጵያዊነት የአፍካዊነት የጥቁርነት ቁስል። የሕሊና ግርፋቴን ነው ያለቀስኩ ይቅርታ ካለቀስኩ ብዙ ጊዜየ ነው"። ብሎኝ ዝም እንዳለ በቃን አልኩት እንለያይ በሚቀጥለው ግንኙነታችን የቀረኘን አብሮን ታግሎ የተሰዋውን የከሊፋን ታሪክ እንደምነግረው ተሰማምተን በንጋቱ ተቃጥረን ተለያየን።

ይቀጥላል

አጅሬው ዘብሔረ መርካቶ (ከመርካቶ)